# ነገም ሌላ ቀን ነው

**ጻቃ (ከዓለም ገና)**

ባለፈው ሣምንት ላይ ነው ከአንድ ጓደኛዬ ጋር በድንገት ተገናኘንና ቡና ሻይ ለማለትና ትንሽ ለመጨዋወት በአቅራቢያው ወደሚገኝ አንድ ካፌቴሪያ ጐራ ያልነው፡፡ መቼም የብዙዎች ሰሞነኛ እንዳውም የወራት ማለት ይቻላል ወሬና ጨዋታ ሁሉ በምርጫው ሂደትና ውጤት ዙሪያ የሚያጠነጥን ነበርና ከጓደኛዬ ጋርም ይህን አንስተን አንዳንድ ሀሳቦችን መለዋወጣችን አልቀረም፡፡

ታዲያ ጓደኛዬ ከምርጫው ውጤት ጋር በተያያዘ ‹‹የዚች አገር ቀጣይ የአምስት ዓመት የፖለቲካ ጉዞ ምን ሊሆን ይችላል አለኝ? ጥያቄውን በጥቅል መልኩ ያቀረበው ስለነበር ትንሽ ዘርዘር አድርጎ መግቢያ ቀዳዳ እንዲያመላክተኝ በማሰብ እንዴት ማለት? ›› ብዬ ጠየኩት፡፡ ‹‹እንዴት ማለትማ እንግዲህ ምርጫውን ሙሉ ለሙሉ ሊባል በሚችል ደረጃ አንድ ፓርቲ ኢህአዴግ ስላሸነፈ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ቀጣይ ተሳትፎ ምን ሊሆን እንደሚችል ሳስብ ከጨዋታ ውጭ የሆኑ ይመስለኛል›› አለ፡፡ እኔም ትንሽ አሰብ አድርጌ በፓርላማ መቀመጫ አጡ ማለት እኮ በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ ዓላማቸውን ማራመድና መንቀሳቀስ አይችሉም ማለት እንዳልሆነ ላብራራለት ሞከርኩ፡፡ በእርግጥም መሠረተ ሀሳቡን ይቀበለው እንጂ ጓደኛዬ የሰጠሁት ሀሳብ ብዙም የተመቸው አልመሰለኝም፡፡ ሆኖም ውይይታችንን ሌላ ጊዜ እንደምንቀጥል ተነጋግረንና ልዩነት እንኳ ቢኖረን በመቻቻል መርህ ሀሳቡን እንደማከብርለትና እንደሚያከብርልኝ እንዲያውም በውይይታችን ገፍተንበት መተማመን እንደምንፈጥር ተነጋግረን ተለያየን፡፡

አዎ ኢ.ህአዴግ የዘንድሮውን ምርጫ እጅግ በላቀ የድምፅ ብልጫ አሸንፏል፡፡ ይህ እውነት ነው፣ አብዛኛው ህዝብ ኢ.ህአዴግን የመረጠውም ያልመረጠውም፣ የደገፈውም ያልደገፈውም ውጤቱን አምኖ በመቀበል ላይ ችግር ያለበት አይመስልም፡፡

በምርጫ ውድድር ሁሉም አሸናፊ ሆኖ የህዝብ የሥልጣን ውክልናን አይዝም፡፡ የአንደኛው ወገን ዓላማ አብላጫ ድምፅ ማግኘቱ የግድ ነው፡፡ ለዚህም ነው ባለፈው ግንቦት 15/2002 በተደረገው አገር አቀፍ ምርጫ አብላጫ የህዝብ ድምፅ ያገኘው ኢ.ህአዴግ ለቀጣዮቹ አምስት ዓመታት አገሪቱን ለመምራት የሚያስችለውን መንግሥታዊ ሥልጣን ሊረከብ በዝግጅት ላይ የሚገኘው፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ይፋ ባደረገው ጊዜያዊ የምርጫ ውጤት መሠረት ኢ.ህአዴግ በሰፊ የድምፅ ልዩነት ተቃዋሚዎችን ማሸነፉ ከተገለፀ በኋላ ተቃዋሚዎች በፓርላማ ያላቸው መቀመጫ ምንም በሚባል ደረጃ መገኘቱ አንዳንድ ወገኖችን ሥጋት ውስጥ እንደከተታቸው ማድመጥ ችያለሁ፡፡ ይህ ሥጋታቸውም የመነጨው ፓርላማው ያለ ተቃዋሚ በአንድ አሸናፊ ፓርቲ ኢ.ህአዴግ ብቻ የሚመራ በመሆኑ የተቃዋሚዎችን ተሳትፎ በከፍተኛ ደረጃ ያዳክማል ከሚል እሳቤ እንደሆነም ይደመጣል፡፡ ከዚህም ባለፈ በዚህ የምርጫ ውጤት ምክንያት በፓርላማ ውስጥ የአንድ ፓርቲ አምባገነንነት ይሰፍናል የሚል አመለካከትም ይንፀባረቃል፡፡

በመሠረቱ በኢፌዴሪ ህገ መንግሥት አንቀጽ 56 ላይ የፖለቲካ ሥልጣን በሚለው ሥር፣ ‹‹በምክር ቤት አብላጫ መቀመጫ ያገኘ የፖለቲካ ድርጅት ወይም ጣምራ ድርጅቶች የፌዴራሉን መንግሥት የህግ አስፈፃሚ አካል ያደራጃል/ያደራጃሉ/፣ ይመራል/፣ ይመራሉ፡፡›› በሚል ተደንግጓል፡፡ እንግዲህ ኢህአዴግ በነፃና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ያገኘውን የህዝብ ድምፅ መሠረት ያደረገ የፓርላማ መቀመጫ ይዞ ሥልጣን የመረከቡ ጉዳይ የሚመነጨው ከዚህ ህግ ነው፡፡ ህገ መንግሥታዊ ሥርዓቱም የሚያስተናግደው ይህንኑ ስለሆነ በዚህ ላይ ክርክር የሚያስነሳ አንዳችም ሁኔታ አይኖርም፡፡

በበኩሌ ተቃዋሚዎች የተሻለ የህዝብ ድምፅ አግኝተውና በፓርላማ ውስጥ ግምት የሚሰጠው መቀመጫ ኖሯቸው ተሳትፎአቸው ቢጎለብት ፋይዳው የበለጠ ሊሆን እንደሚችል አምናለሁ፡፡ ሆኖም ግን አብላጫው ህዝብ ይበጀኛል ያለውን ፓርቲ የመረጠ በመሆኑ የህዝብ ድምፅ መከበርና ህገ መንግሥታዊ ሥርዓቱ በሚፈቅደውና በሚያዘው መሠረትም መፈፀም ስላለበት በዚህ ላይ ሌላ ድርድር ውስጥ የሚገባበት ወይም ጥያቄ የሚነሳበት ጉዳይ ሊኖር አይችልም፡፡ አብዛኛው የፓርላማ መቀመጫ/ሙሉ ለሙሉ ማለት በሚያስችል ደረጃ/ በኢህአዴግ እንዲያዝ ያደረገው የህዝብ ነፃ ምርጫ ውጤት መሆኑን አምኖ መቀበል የግድ ይላል፡፡

እኔን እንደሚመስለኝ እዚህ ላይ በዋናነት መነሳት ያለበት ነጥብ ህዝቡ ከቀረቡለት አማራጮች መካከል የቱን ደገፈ የሚለው ነው፡፡ ይህን ጥያቄ በግልጽና በትክክል እንመልስ ካልን ህዝቡ በነፃ ምርጫው አረጋግጦ ድምፁን የሰጠው አንድ ፓርቲ አለ፣ ይህም ኢህአዴግ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ዘንድ ህዝብ የመረጠው ዓላማ ተፈፃሚ

እንዲሆንለት በፓርላማ ውስጥ ያለው የህዝብ ውክልና መቀመጫዎች በኢህአዴግ እንዲያዙ የግድ ይላል፡፡ ከአሸናፊው ፓርቲ ጀርባ እኮ የመረጠውን አብላጫ ህዝብ ነው ማየት ያለብን፡፡ በነፃና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ከሌሎች በርካታ ፓርቲዎች ጋር ተወዳድሮ የህዝብ ሥልጣን ውክልና መያዝ የህዝብን ነፃ ምርጫና ዓላማ ተፈፃሚ ማድረግ የአንድ ፓርቲን ፈላጭ ቆራጭነትን፣ አድራጊ ፈጣሪነትን ወይም አምባገነንነትን የሚያመለክት ተደርጐ መወሰድ የለበትም፤ለዚህም ፍትኃዊ መመዘኛ አይኖርም፡፡ ከዚህ ይልቅ በግልጽ ሊታይ የሚችለው የህዝብ የበላይነትና ወሣኝነት ብቻ ነው ፡፡

የመድበለ ፓርቲ ህገ መንግሥታዊ ሥርዓት ተዘርግቶ ሁሉም በመሰለውና ይጠቅማል በሚለው መንገድ የፖለቲካ ዓላማ ይዞ በነፃነት ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ እያደረገ ያለበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡ ይህን መሰረት ባደረገ ነፃ የህዝብ ምርጫ ሂደት በተከናወነበት ሁኔታ የአንድ ፈላጭ ቆራጭ ፓርቲ ሥርዓት እየተፈጠረ ነው ብሎ ማሰብ ከቶም ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ምክንያታዊ ሊሆንም አይችልም፡፡ የአገሪቱ ህገ መንግሥትም ይህ እንዲሆን አይፈቅድም፡፡ እስካሁን የተጓዝንበት የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደትም እያረጋገጠ የመጣው ይህንኑ ሀቅ ነው፡፡

በዚህ ነፃ ምርጫ ላይ አብላጫውን እንዲያውም ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ የህዝብ የሥልጣን ውክልናን አንድ ፓርቲ መያዙ የህዝቡ ነፃ ፍላጐትና ምርጫ መገለጫ ከመሆን ባለፈ ሌላ ትርጉም ሊሰጠው የሚገባ አይመስለኝም፡፡ በማንኛውም መመዘኛ ቢታይ ዞሮ ዞሮ የህዝብ ነፃ ውሣኔ እስከሆነና ህገ መንግሥታዊ ሥርዓቱ

እስከፈቀደ ድረስ ውጤቱን አምኖ በመቀበል ለአፈፃፀምና ለውጤታማነቱ የራስን ድርሻ መወጣት ተገቢ ነው የሚሆነው፡፡ ሌላ አቋራጭ መንገድ ወይም አማራጭ ሊኖር አይችልም፡፡ የህዝብ ውሣኔ ነውና ይህ መከበር ይኖርበታል፡፡

አንድ አሸናፊ ፓርቲ በውድድር አሸንፎ አብላጫ የፓርላማ መቀመጫ መያዝና ውጤቱንም አስከብሮ በተከታታይ የምርጫ ውድድሮች አሸናፊ ሆኖ ሥልጣን መያዝ በሀገራችን ብቻ ያጋጠመ ልዩ ክስተት ተደርጐ አይወሰድም፡፡ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የበለፀገና የዳበረ ልምድ አላቸው በሚባሉ አገራትም ውስጥ የተለመደና ያለ ክስተት ነው፡፡ በዚህ ዓይነት ለተከታታይ የምርጫ ዙሮች ሥልጣን ላይ የቆዩና አሁንም ያሉ ፓርቲዎች አሉ፡፡

እዚህ ላይ አንድ የሚገርመኝን ትዝብት ማንሳት ወደድኩ፡፡ ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ በአገራችን እስካሁን አራት ስኬታማ ምርጫዎች ተደርገዋል፡፡ በነዚህ ነፃና ዴሞክራሲያዊ ምርጫዎችም ኢ.ህአዴግ የህዝብ ድምፅ ይሁንታን አግኝቶ አሸናፊ መሆን ችሏል፡፡ በእርግጥ ከአንደኛው እስከ ሦስተኛው ዙር ምርጫ ተቃዋሚዎች በፓርላማ የነበራቸውን መቀመጫ እያሳደጉ መጥተው ነበር፡፡ ሆኖም በአራተኛው ምርጫ ላይ ግን የፈለጉትን ሳያገኙ ቀርተዋል ወይም አልተሳካላቸውም፡፡ ድል ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ወደ ኢ.ህአዴግ አጋደለ፣ ይህም የህዝብ ፍላጐትና ውሣኔ ነው፡፡

ታዲያ ኢ.ህአዴግ ከመጀመሪያው እስከ አራተኛው ዙር ድረስ ያገኘውን የምርጫ ስኬትና ድል ከተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል አንዱ ወይም ሌላው አግኝቶ ቢሆን

ኖሮ፣ የአንድ ፓርቲ አምባገነንነት እየነገሰ ነው በሚል በአንዳንድ ኃይሎች እየተነገረ ያለውን ዓይነት ትርጉም ለራሱ ስለመስጠቱ እጅግ እጠራጠራለሁ፡፡ በእርግጠኝነት ይህን የሚያነሳ ፓርቲ እንደማይኖር ደፍሬ መናገር እችላለሁ፡፡ ኢህአዴግ በመሆኑ ብቻ ግን እንዴት ይህ ትርጉም ሊሰጠው እንደቻለ አንዳችም ምክንያታዊ ትንታኔ ሲቀርብበት አይታይም፡፡ ሊቀርብበትም የሚያስችል አሳማኝ ምክንያት ያለ አይመስለኝም፡፡

በምርጫ ላይ ማሸነፍንና መሸነፍ የአንድ ሣንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው፡፡ ተሸናፊው የያዘው ዓላማ የአብላጫውን ህዝብ ይሁንታ ባለማግኘቱ ብቻ ተሸናፊ መሆኑን አምኖ መቀበል የግድ ይለዋል፡፡ ለሽንፈቱ መንስኤ የሆነ ድክመቱን አርሞና ስትራቴጂ ነድፎ የተሻለ አማራጭ ይዞ ለመቅረብ ራሱን ማዘጋጀት ብቻ ነው የሚጠበቅበት፡፡ በአንደኛው ዙር ያልተሳካለት በሌላኛው ዙር ሊሳካለት ይችላል፡፡ በወቅቱ አሸናፊ ከሆነው ፓርቲና ህዝቡ ፍላጎቱን ካንፀባረቀበት ሁኔታም እኮ በመነሳት ትምህርትና ልምድ ይቀሰማል፡፡ አሸናፊው ፓርቲ የአብላጫውን ህዝብ ድምፅ እንደመወከሉ እውቅናና ከበሬታ ሊሰጠው ይገባል፣ ምክንያቱም ሕዝብን ማክበር ነውና፡፡

ነገርን ነገር ያነሳዋልና ከምርጫው ፍፃሜ በኋላ ካስተዋልኳቸው ክስተቶች መካከል አንድ ሁለቱ የበለጠ ማርከውኛል ወይም በዘመነኞቹ አነጋገር ተመችተውኛል፡፡ አንደኛው በርካታ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አሸናፊውን ፓርቲ እንኳን ደስ ያለህ ማለታቸው ነው፡፡ ለአገራችን አዲስ ፖለቲካዊ ባህል በመሆኑ አድንቄአቸዋለሁ፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በምርጫው ማግሥት ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በመስቀል

አደባባይ ለተሰበሰበው ህዝብ ንግግር ሲያደርጉ ያስተላለፉት አንድ መልዕክት ነው፡፡ ይህም ተቃዋሚ ፓርቲዎች በፓርላማ መቀመጫ ኖራቸውም አልኖራቸውም፣ ቁጥሩ ይነስም ይብዛ፣ እነሱን የመረጠው ህዝብ ድምፅ መደመጥ ስላለበት በዋና ዋና አገራዊ ጉዳዮችና አጀንዳዎች ላይ እንደሚያወያዩቸውና እንደሚያሳትፏቸው ቃል የገቡት፡፡

ይህ ታዲያ የእርቀ አስተዋይነትና የፖለቲካ መቻቻል የተንፀባረቀበት አዲስ ዓይነት የፖለቲካ ባህል በመሆኑ ታላቅ ከበሬታና አድናቆት የሚሰጠው ሆኖ ተሰምቶኛል፡፡ በዚህም የኢህአዴግ ደጋፊም ተቃዋሚም ሆነ ሌላው የህብረተሰብ ክፍል በጋራ የሚስማሙበት ነጥብ እንደሆነ በግሌ በተለያዩ አጋጣሚዎች ካገኘኋቸው መረጃዎች መረዳት ችያለሁ፡፡ ኢህአዴግም ይህን ቃሉን ጠብቆ ተግባራዊ ያደርጋል የሚል ጠንካራ ዕምነት በብዙዎች ዘንድ አድሯል፡፡

ቀድሞም ቢሆን እኮ ተቃዋሚዎች በፓርላማው በነበራቸው አነስተኛ መቀመጫ ምክንያት የመደመጥ ዕድል ነበራቸው እንጂ ማንኛውም ውሣኔ የሚወሰነው ያው እንደሚታወቀው በአብላጫ ድምፅ ነበር፡፡ በእርግጥ በፓርላማ በነበራቸው ተሳትፎም በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ አንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የሚሰጧቸው አዎንታዊና ገንቢ ሀሳቦችና ድጋፎች ግምት ውስጥ የሚገቡበትና የሚካተቱበት ሁኔታ ነበረ፡፡ ተቃዋሚዎች የፓርላማ ውክልና ባለማግኘታቸው በዚህ ረገድ በተወሰነ ደረጃ ሊፈጠሩ የሚችሉ እጥረቶችን ወይም ክፍተቶችን ለመሙላት ኢህአዴግ ቀደም ብሎ ያሰበበት መሆኑ መገለጹ ታላቅ ፖለቲካዊ እርምጃ ነው፡፡ ኢህአዴግ በቀጣይ እፈጥረዋለሁ ባለው አሳታፊ መድረክ ላይ ተቃዋሚዎች የአገራዊ ጥቅም ማስከበር

ዓላማን ለማሳካት የቀረበላቸውን ጥሪ ከልብ አምነው በመቀበል እንደሚተገብሩት ትልቅ የህዝብ ተስፋ አለ፡፡ ያለፉ ስህተቶችን ዓይነት አሁን መድገም አይጠበቅም፣ አይገባምም፡፡ ስለዚህ በዚህ ረገድ ተቀራርቦ መስራቱ ለሀገርና ለህዝብ ትልቅ ጠቀሜታ አለው ብዬ አምናለሁ፡፡

እንግዲህ ለጽሁፌ መቋጫ የሚሆነው ሀሳብ የሚያጠነጥነውም እዚህ ላይ ነው፡፡ እስካሁን ይዘነው የዘለቅነው ህገ መንግሥታዊ ሥርዓት ቀጣይነቱ በተረጋገጠበት ሁኔታና ይህን መሰረት አድርጎ በተካሄደ ነፃ፣ ሰላማዊ፣ ፍትሀዊና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ሥልጣን የያዘ አንድ ፓርቲ በምንም ዓይነት መመዘኛ ቢሆን አምባገነንነትን ያመጣል ብሎ ማሰብ መሠረታዊ ስህተት ነው፡፡ ተቃዋሚዎችም እኮ ቢሆኑ ለምርጫ ውድድር የቀረቡት ህገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ተቀብለውና አክብረው ነው፡፡ ይህ ከሆነ ዘንድም የህዝቡን ይሁንታ አግኝቶ ሥልጣን የሚይዘው ፓርቲ ተግባራዊ የሚያደርገውና በጥቅሉ ሲታይም የሚተረጉመው ህገ መንግሥቱን ነው፡፡ ኢህአዴግ በህዝብ ነፃ ምርጫ በተደጋጋሚ የምርጫ ዙሮች ሥልጣን መያዙ አንድ ጊዜ አምባገነናዊነትን ይፈጥራል፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ የቻይናን ሞዴል ይከተላል ሊያስብል የሚችል ምንም ዓይነት የመከራከሪያ ነጥብ ሊያስነሳ የሚችል አይሆንም፡፡ ህዝቡ እኮ በነፃነት እንደመረጠው ማረጋገጫ ሰጥቷል፡፡

ኢህአዴግ ህዝቡን እመራበታለሁ ብሎ የነደፋቸው ፖሊሲዎች የሚመነጩት በመሰረታዊነት ከህገ መንግሥቱ ነው፡፡ የአገራችን ህገ መንግሥት የተቀረፀው በአገራችን ነባራዊ ሁኔታ ላይ ተመስርቶ ስለሆነ የራሱ የሆነ ባህሪይና መገለጫ ያለው እንጂ ከቻይና ወይም ከሌላ አገር የተገለበጠ አይደለም፡፡ የአንድ አገር ህገ

መንግሥት በተለያዬ መልኩ በአንድ ወይም በሌላ የሚመሳሰልበት ሁኔታ ቢኖር እንኳ ይህ ዓለም አቀፋዊ አሰራር ነው ሊሆን የሚችለው፡፡ ለምሳሌ በሰብአዊ መብቶች አጠባበቅና በፌዴራል ሥርዓቱ አወቃቀር ላይ ከሌላ አንድ አገር ህግ ጋር መመሳሰሎች ቢኖሩም እንኳ ጠቃሚ ዓለም አቀፋዊ ተሞክሮዎች ተወስደው ሊሆን ስለሚችል አዎንታዊ ነው፡፡ የአገራችን የመንግሥት ሥልጣን አያያዝ በህገ መንግሥቱ ላይ በተደነገገው መሠረት ብቻ ስለሆነ የሌላ አገርን የመንግሥት አወቃቀር ሞዴል ተግባራዊ ማድረግ አያስችልም፡፡

ስለሆነም ተቃዋሚ ፓርቲዎች በህገ መንግሥታዊ ሥርዓቱ ታቅፈው በ4ኛው ዙር የምርጫ ውድድር እንደመሳተፋቸው ህዝቡ በነፃ ምርጫው ያረጋገጠውን ውጤት ሊቀበሉ ግድ ይላቸዋል፡፡ ከዚህም ጋር በቀጣይ በሚያገኙት ዴሞክራሲያዊ መድረክ ሰላማዊና ህጋዊ ተሳትፎአቸውን ለመቀጠል ዝግጁነቱና በጎ ፈቃደኝነቱ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ጉድለቶቻቸውን አርመውና የህዝብ ፍላጎትን መሰረት አድርገው በህግ አግባብ በሰላም እስከተንቀሳቀሱ ድረስ ነገም ሌላ ቀን ነውና ለቀጣዩ ውድድር ራሳቸውን ዝግጁ አድርገው የማይቀርቡበት ምንም ምክንያት አይኖርም፡፡ ለዚህም ከወዲሁ ወገብን ጠበቅ ማድረግ አይሻልም ትላላችሁ?